# የጥራት መስፈርቶችን ስለማያሟላ የዕፅዋት ዘር አጠቃቀም እና አወጋገድ መመሪያ

መመሪያ ቁጥር 465/2013

## መግቢያ

በአገሪቱ የዘር ጥራትን በማረጋገጥ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለሁለት ተከታታይ አሥርት ዓመታት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከዚህም ጥረት መካከል የሚጠቀሰው ዘር በማምረት ሂደት በማሳና በላቦራቶሪ የሚካሄደው የዘር ጥራት ቁጥጥር አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ጥረት ውጤታማ ለማድረግ ፌደራልና ክልሎች ከፍተኛ በጀት በመመደብ ስራውን ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡

ከዓመታዊ በጀታቸውም ከፍተኛ ካፒታል በመመደብ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ መስፈርት መሠረት በመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራ በመስራት ያለፉና የወደቁ ማሳዎችን በመለየት ካለፉ ማሳዎች የተሰበሰበውን ዘር ለቀጣይ የዘር ጥራት ፍተሻ ሲያዘጋጁ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ የወደቁ ማሳዎችንም መውደቃቸውን የሚያረጋግጥ ሪፖርት ለአምራቾችና ለሚመለከታቸው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሁሉ በሪፖርት የማሳወቅ ሥራ ይሠራል፡፡ የመስክ የጥራት ቁጥጥር መስፈርት አሟልቶ ካለፉና ተበጥሮ ከተዘጋጀ የዘር ሎት ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ ደረጃ ፍተሻ በማካሄድ የዘር ጥራትን በማረጋገጥ ለወደቁ ሎቶች መውደቃቸውን የሚገልጽ ሪፖርት ለአምራቾች ይቀርባል፡፡ ይህ ሁሉ ጥረት ቢደረግም ለወደቁ ማሳዎችና ሎቶች ከስርጭቱ ስለመወገዳቸው የሚገልጽ ሪፖርት ከመጻፍ ባለፈ ከወደቁ ማሳዎች የተገኘውን ዘርና የወደቁ ሎቶች ከግብይት ሥርዓቱ መወገዱን የሚያረጋግጥ አሠራር ስላልነበረ ችግሩን በተግባር ለመፍታት ይህንን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

### 1. አውጭው ባለሥልጣን

የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ስለ ዕፅዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 በአንቀፅ 27/2 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 16(1)(2)(3) የተደነገገውን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የጥራት መስፈርቶችን የማያሟላ የዕፅዋት ዘር አጠቃቀም እና አወጋገድ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር**465/2013**ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

## 3. ትርጓሜ

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ:-

3.1. "መደበኛ የዘር ሥርዓት" ማለት በሀገሪቷ በወጣው የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የተመዘገበ የተሻሻለ ዝርያ ዘር በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ከዘር ማሣ ዝግጅት እስከ ግብይት ድረስ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሠራር ሂደት ነው፤

3.2. "የተሸጋጋሪ /Intermediate/ የዘር ሥርዓት" ማለት በመደበኛውና በኢ-መደበኛው የዘር ሥርዓት መካከል የሚገኝ ነው፤

3.3. "ኢ-መደበኛ የዘር ሥርዓት" ማለት የተመዘገበ ወይም የአካባቢ ዝርያ /ነባር ዝርያ/ በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም በወጣው የዘር ደረጃ (መስፈርት) መሠረት ቁጥጥር ሳይደረግበት አርሶ አደሩ እርስ በርስ የሚያደርገው የዘር ልውውጥ ነው፤

3.4. "የዘር ሎት" ማለት ወጥነት ያለው በአካል ሊለይ የሚችልና መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ነው፤

3.5. "የወደቀ የዘር ሎት" ማለት ከአምራች፣ ከዘር አከፋፋይ፣ ከአስመጪ፣ ከላኪ ወይም ከቸርቻሪ ከተወሰደ ናሙና ዘር ላይ በላቦራቶሪ በተደረገ የዘር ጥራት ፍተሻ ዝቅተኛውን የጥራት መስፈርት ያላሟላ ዘር ነው፤

3.6. "የውስጥ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር" ማለት ዘር አምራቹ ያባዛውን ዘር በመስክና በላቦራቶሪ ደረጃ በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት በዘር ጥራት መስፈርት መሠረት የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

3.7. "ዘር አከፋፋይ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኖሮት፣ የኢትዮጵያ ዘር ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉና ምንጫቸው የታወቁና የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያ ዘሮችን በመጋዘን በማከማቸት ለቸርቻሪዎች ወይም በስፋት ለሚያመርቱ ተጠቃሚዎች በጅምላ የሚሸጥ ሰው ነው፤

3.8. "ዘር ቸርቻሪ" ማለት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለውና ከዘር አከፋፋይ ወይም አምራች የሚረከበውን የዕፅዋት ዘር ጥራቱ እንደተጠበቀ ለተጠቃሚ በችርቻሮ እስከ ዝቅተኛው መጠን መያዣው ሳይከፈት የሚሸጥ ሰው ነው፤

3. ትርጓሜ

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ:-

3.1. "መደበኛ የዘር ሥርዓት" ማለት በሀገሪቷ በወጣው የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የተመዘገበ የተሻሻለ ዝርያ ዘር በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ከዘር ማሣ ዝግጅት እስከ ግብይት ድረስ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሠራር ሂደት ነው፤

3.2. "የተሸጋጋሪ /Intermediate/ የዘር ሥርዓት" ማለት በመደበኛውና በኢ-መደበኛው የዘር ሥርዓት መካከል የሚገኝ ነው፤

3.3. "ኢ-መደበኛ የዘር ሥርዓት" ማለት የተመዘገበ ወይም የአካባቢ ዝርያ /ነባር ዝርያ/ በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም በወጣው የዘር ደረጃ (መስፈርት) መሠረት ቁጥጥር ሳይደረግበት አርሶ አደሩ እርስ በርስ የሚያደርገው የዘር ልውውጥ ነው፤

3.4. "የዘር ሎት" ማለት ወጥነት ያለው በአካል ሊለይ የሚችልና መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ነው፤

3.5. "የወደቀ የዘር ሎት" ማለት ከአምራች፣ ከዘር አከፋፋይ፣ ከአስመጪ፣ ከላኪ ወይም ከቸርቻሪ ከተወሰደ ናሙና ዘር ላይ በላቦራቶሪ በተደረገ የዘር ጥራት ፍተሻ ዝቅተኛውን የጥራት መስፈርት ያላሟላ ዘር ነው፤

3.6. "የውስጥ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር" ማለት ዘር አምራቹ ያባዛውን ዘር በመስክና በላቦራቶሪ ደረጃ በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት በዘር ጥራት መስፈርት መሠረት የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

3.7. "ዘር አከፋፋይ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኖሮት፣ የኢትዮጵያ ዘር ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉና ምንጫቸው የታወቁና የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያ ዘሮችን በመጋዘን በማከማቸት ለቸርቻሪዎች ወይም በስፋት ለሚያመርቱ ተጠቃሚዎች በጅምላ የሚሸጥ ሰው ነው፤

3.8. "ዘር ቸርቻሪ" ማለት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለውና ከዘር አከፋፋይ ወይም አምራች የሚረከበውን የዕፅዋት ዘር ጥራቱ እንደተጠበቀ ለተጠቃሚ በችርቻሮ እስከ ዝቅተኛው መጠን መያዣው ሳይከፈት የሚሸጥ ሰው ነው፤



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of ... & Natural Resources

3.9. "መለያ ምልክት" ማለት ማናቸውም በዘር መያዣ ዕቃ ላይና ውስጥ የዘሩን ምንነት ለመለየት የተቀመጠ ወይም የተለጠፈ የጽሑፍ ወይም የሥዕል መግለጫ ነው፤

3.10. "ለዘርነት የማይውል ምርት ማሸግ" ማለት ከወደቀ ዘር ማሳ የተገኘ ምርት ወይም በላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ የወደቀ የዘር ሎት በተለየ መጋዘን ውስጥ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ በተቆጣጣሪው አካል ማሸግ ማለት ነው፤

3.11. "ጥራቱ የተገለጸ ዘር" ማለት አነስተኛ ይዞታ ባላቸው በተደራጁና ተመዘገቡ ወይም በተመዘገቡ አርሶአደሮች አማካኝነት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ የተመረተ ዘር ነው፤

3.12. "ውሳኔውን የሰጠው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል" ማለት የተመዘገበ ዝርያን ጥራት ለማረጋገጥ ሥልጣን ያለው አካል ነው፤

3.13. "ማስወገድ" ማለት የወደቀን ዘር ለዘር ሽያጭ አገልግሎት እንዳይውል እና ዘሩ ለሰው፣ ለእንስሳት እና ለአካባቢ አደጋ እንደማይኖረው ሲረጋገጥ አምራቹ በራሱ ማሳ እንዲዘራው ወይም ለሰው ምግብነት ወይም ለመኖነት እንዲውል የሚያስችል ይህ ካልሆነ ግን ማቃጠልን ወይም መቅበርን ያመለክታል ፤

3.14. "ፈርነስ" ማለት በከፍተኛ ሙቀት ኃይል የወደቀን ዘር ለማቃጠል የሚያገለግል የኤሌክትሪክ ምድጃ ነው፤

3.15. "አስወጋጅ ኮሚቴ" ማለት የወደቀን ዘር ከዘር ስርጭትና ግብይት ሥርዓት እንዲወጣና እንዲወገድ ለማድረግ ከተለያዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ተውጣጥቶ የሚቋቋም አካል ነው፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

4.1 በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

4.1.1 በመደበኛው የዘር ሥርዓትና ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡና የዘር ጥራት ደረጃ የወጣላቸው ሰብሎችና ዝርያዎች ላይ፤

4.1.2 በመመረት ሂደት እያለ በተካሄደ የዘር ጥራት ቁጥጥር ከወደቀ ማሳ የተሰበሰበ ዘር ላይ፤

4.1.3 ተመርቶና ተዘጋጅቶ በላብራቶሪ ፍተሻ የወደቀ የዘር ሎት ላይ፤

4.1.4 በድህረ-ቁጥጥር ፍተሻ የወደቀ ዘር ላይ ነው፡፡

4.2. ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.1 የተገለጸው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው፡-

ሀ/ ማንኛውም ሰው ከእርሻ ምርቱ ጠብቆ በሚይዘውና በሚጠቀምበት ዘር፤

ለ/ በአርሶ አደሩ መካከል የሚደረግ የዘር ልውውጥ፤

ሐ/ በደን ዘር፤

መ/ ለምርምር ሥራ የሚውል ዘር፡፡

5. **የመመሪያው ዓላማ**

5.1 በዘር ጥራት ቁጥጥር ሂደት የወደቀ ዘር በገበያ ላይ እንዳይውል ለመከላከል

5.2 ለዘር ተጠቃሚው ዋስትና ለመስጠት፤

5.3 በህገ ወጥ መንገድ የሚደረገውን የዘር ግብይት ለመከላከል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በማሳ ላይ የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ስለማያሟላ ዘር አወጋገድ

6. በመስክ ጥራት ቁጥጥር አንድ ማሳ እንደወደቀ የዘር ኢንስፔክተሩ ያቀረበውን ሪፖርት የሚመለከተው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል መርምሮ ውሳኔውን ካፀደቀ በኃላ ማሳው የጥራት ደረጃ መስፈርቶች አለማሟላቱን የሚገልጽ ሪፖርት ለአምራቹ እና አግባብ ላለው የክልል ባለሥልጣን ይልካል፤

7. የመስክ ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተር ካቀረበው የወደቀ ማሳ ሪፖርት ጋር በጂ.ፒ.ኤስ የተደገፈ ፎቶ (photo-tagged)፣ በጂ.ፒ.ኤስ መረጃ የተደገፈን የካርታ ኮኦርዲኔት (ለወደቀውና ለዋናው ማሳ) እና የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር ቅጽ አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፤

8. አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን የቀረበው ሪፖርት ቅሬታ እስካልቀረበበት ድረስ ለውሳኔው ተግባራዊነት ይተባበራል::

9. አምራቹ ከወደቀው ማሳ የሰበሰበውን ምርት ለምን አገልግሎት እንደሚያውለው ውሳኔውን ከሰጠው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ጋር በተዘጋጀው የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር ቅጽ ላይ ይፈራረማል::

10. ከወደቀው ማሳ የተገኘው ምርት ተወቅቶ በጆንያ ከተከተተ በኋላ ይታሸግና ለዘርነት የማይውል የሚል መለያ ምልክት ይደረግበታል::

11. አምራቹ የመስክ ጥራት ቁጥጥር መስፈርት ያላሟላውን ዘር በራሱ ማሳ የሚጠቀም ከሆነ ውሳኔውን ለሰጠው ተቆጣጣሪ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ የወደቀውንም ዘር ለሌላ አርሶ አደር ለዘርነት እንዲውል አሳልፎ መሸጥ አይችልም::

12. ውሳኔውን የሰጠው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ዘሩ የወደቀበት ምክንያት ለሰው፣ ለእንስሳት፣ለዕፅዋት፣ ለአካባቢ ጥበቃ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ የወደቀው ዘር የተቆጣጣሪው አካል ተወካይና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል ይደረጋል::

13. ከወደቀው ማሳ የተገኘው ምርት ሲሰበሰብ፣ ሲከማች፣ ሲወቃ እና ከዘር አገልግሎት ውጭ ለሌላ ተግባር ሲውል የዘር ጥራት ተቆጣጣሪው አካል ተወካይ ባለሙያ መገኘት አለበት::

14 የተጠየቀውን የዘር ደረጃ በመስክ ጥራት ቁጥጥር መስፈርትን የማያሟላ ከሆነ ከታለመለት ደረጃ ዝቅ ባለ የዘር ትውልድ ደረጃዎች አንዱን አሟልቶ ከተገኘ የመስክ ጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

15. ከላይ በአንቀጽ 14 የተገለጸው እንደጠበቀ ሆኖ ደረጃው የተሻሻለው የወደቀ ማሳ ዘር የሚሰበሰበው የተቆጣጣሪው አካል ባለሙያ በተገኘበት መሆን አለበት::

16. አምራቹ ከወደቀው ዘር ማሳ ተወቅቶ የተገኘውን ምርት ምልክቱ እንደተለጠፈ ለምግብነት ወይም መኖነት መጠቀም ለሚፈልጉ አካላት የተቆጣጣሪው አካል ተወካይ በተገኘበት መሸጥ ይኖርበታል::

17. የዘር ጥራት ተቆጣጣሪው አካል የወደቀው ዘር ለምግብነት ወይም መኖነት እንዲውል የተወሰነውን ከወደቀ ማሳ የተገኘን ምርት ለተባለው ጉዳይ መዋሉን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል::

18. ከወደቀ ማሳ የተገኘን ምርት በመፍጨት ወይም በመቁላት ወይም በመቀቀል ከዘር ሥርጭት ሥርዓቱ እስካልተወገደ ድረስ ማንኛውም ሰው ‹‹ለዘርነት የማይውል›› የሚለውን መለያ ምልክትና የከረጢት ስፌት ማላቀቅ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

19. በመስክ የዘር ጥራት መስፈርትን ካላሟላ ማሳ የተሰበሰበ ዘር አወጋገድን አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ አካል በሚሰጠው የቅርብ ክትትልና ውሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል::

20. ከወደቀ የዘር ማሳ የተገኘን ምርት ከስድስት ወር በላይ መጋዘን ውስጥ ማቆየት አይፈቀድም፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ምርቱ ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ በላይ በመጋዘን ከቆየ በተቆጣጣሪው አካል ለአስወጋጅ ኮሚቴ በሚቀርብ ሪፖርት መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## በላቦራቶሪ የዘር ጥራት መስፈርቶችን ደረጃ ስለማያሟላ ዘር አወጋገድ

21. አንድ የዘር ሎት ናሙና ተወስዶ በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ ውጤት መሠረት የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን እንደማያሟላ ሲረጋገጥ ውድቅ የተደረገበት የላቦራቶሪ ፍተሻ ውጤት ሪፖርት ለአምራቹ/አዘጋጁ እና አግባብ ላለው ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው የክልል ባለሥልጣን ይላካል::

22. አግባብ ያለው የክልል የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በቀረበው ሪፖርት ቅሬታ እስካልቀረበ ድረስ ለውሳኔው ተግባራዊነት ይተባበራል::

23. የዘር ሎቱ ባለቤት ውሳኔውን ለሰጠው ተቆጣጣሪ አካል በላቦራቶሪ ፍተሻ የወደቀው ዘር ለምን አገልግሎት እንደሚያውለው ወዲያውኑ በደብዳቤ ያሳውቃል::

24. ውሳኔውን የሰጠው ተቆጣጣሪ አካል የዘር ሎቱ የወደቀበት ምክንያት ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት እና ለአካባቢ ጥበቃ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ የወደቀው የዘር ሎት የተቆጣጣሪው አካል ተወካይና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል ይደረጋል::

25. የላቦራቶሪ ጥራት ፍተሻ መስፈርት ያላሟላው የዘር ሎት በዚህ መመርያ በአንቀጽ 24 መሠረት ጉዳት የሚያደርስ ሆኖ ካልተገኘ በላቦራቶሪ የጥራት መስፈርት ደረጃ በሚያሟላውና ቀጥለው ባሉት ተከታይ የዘር ትውልድ በአንዱ ተመድቦ የዘር ጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ይሰጠዋል::

26. በአንቀጽ 24 በተገለፀው መሠረት የወደቀው ዘር ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ የወደቀን የዘር ሎት "ለዘርነት የማይውል" የሚለውን መለያ ምልክት አያይዞ ለምግብነት ወይም ለእንሰሳት መኖነት መጠቀም ለሚፈልጉ አካላት የተቆጣጣሪው አካል ተወካይ በተገኘበት የዘር ሎቱን ባለቤትቱ መሸጥ ይችላል::

27. በላቦራቶሪ ፍተሻ የወደቀው የዘር ሎት ከረጢቶች ላይ "ለዘርነት የማይውል" የሚል መለያ ምልክት ውሳኔውን በሰጠው ተቆጣጣሪ አካል ተደርጎበት በሌላ መጋዝን ተለይቶ እንዲከማች ይደረጋል::

28. የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ መስፈርት ያላሟላን የዘር ሎት የዘሩ ባለቤት የሆነ አካል በራሱ ማሳ ላይ ለዘርነት የሚጠቀም ከሆነ ውሳኔውን ለሰጠው ተቆጣጣሪ አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት::

29. ማንኛውም አካል የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ መስፈርት ያላሟላንና ለዘርነት እንዳይውል የተከለከለን የዘር ሎት ለሌላ ተጠቃሚ ለዘር አገልግሎት እንዲውል አሳልፎ መሸጥ አይችልም::

30. የተቆጣጣሪው አካል ለምግብነት ወይም መኖነት እንዲውል የተወሰነውን የወደቀን ዘር ሎት ለዚህ ተግባር መዋሉን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል::

31. የወደቀን የዘር ሎት በመፍጨት ወይም በመቁላት ወይም በመቀቀል ከዘር ሥርጭት ሥርዓቱ እስካልተወገደ ድረስ ማንኛውም ሰው ለዘርነት የማይውል የሚለውን መለያ ምልክትና የከረጢት ስፌት ማላቀቅ ፈጽሞ የተከለከለ ነው::

32. የወደቀ የዘር ሎት ከስድስት ወር በላይ መጋዝን ውስጥ ማቆየት አይፈቀድም፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ዘሩ ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ በላይ በመጋዝን ከቆየ በተቆጣጣሪው አካል ለአስወጋጅ ኮሚቴ በሚቀርብ ሪፖርት መሠረት እንዲወገድ ይደረጋል::

## ክፍል አራት

## በኬሚካል ታሽቶ በመጋዘን ያደረ ዘር አወጋገድ

33. በኬሚካል የታሸ ዘር አወጋገድን በተመለከተ፤

33.1 በኬሚካል ታሽቶ በመጋዘን ያደረ ዘር የማስወገጃ ዘዴ በእዳሪ መሬት ወይም በሰብል ያልተያዙ ማሳዎች ላይ መዝራት፤ በኬሚካል የታሸው ዘር በቤትና በዱር እንስሳቶች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በዘር ከረጢት ላይ በተገለጸው ጽሁፍ መሰረት ዘሩን በጥንቃቄ መዝራት፤

ሀ/ የምንጠቀመው የዘር መጠን የሀገሪቱ የኤክስቴንሽን ፓኬጅን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ለ/ በኬሚካል የታሸውን ዘር ከ2.5 ሲንቲ ሜትር ጥልቀት በላይ መዝራት፣ ዘሩ በብተና የተዘራ ከሆነ በአግባቡ ከአፈሩ ጋር ማዋሃድ፤

ሐ/ ዘሩ ሲጫንና ሲወርድ የተፋሰሱና በአካባቢው የሚታዩ ዘሮችን በአግባቡ መሰብሰብና በጥንቃቄ ማስወገድ፣ የተመረጠው ቦታ ከውሃ አካባቢ የራቀ መሆን አለበት፤

መ/ ዘሩን ባልታረሰ መሬት፣ በሜዳ ወይም ከእርሻ ቦታ ውጪ መዝራት አይቻልም፤ ይህ ካለሆነ ዘሩ ከአፈሩ ጋር ስለማይዋሃድ የታለመውን ግብ ሳይመታ ለሌላ የአካባቢ ብክለት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

33.2 በኬሚካል የታሸ ዘር ከላይ እንደተገለጸው መሬት ላይ በመዝራት ማስወገድ ካልተቻለ የኬሚካል ባህሪውንና ተያያዥ መረጃዎችን በማየት፤

ሀ/ በሀገሪቱ የተፈቀደ የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ ውስጥ ማስወገድ፤

ለ/ ለሲሚንቶ ፋብሪካ የሀይል ፍጆታ በማዋል ማስወገድ፣

ሐ/ በከፍተኛ ሙቀት የማቃጠያ ዘዴ /ፈርነስ/ በመጠቀም ማስወገድ፤

መ/ በኬሚካል የታሸው ዘር መጠነ ሰፊ ከሆነ ለአልኮል ማብላልያ ሂደት /ለኢታኖል ምርት/ መጠቀም የሚቻል ሲሆን መወሰድ የሚገባቸው ቅድመ ጥንቃቄዎች፦

1/ የኢታኖል ተረፈ ምርትን ለእንስሳት መኖነት መጠቀም አይቻልም፤

2/ በኢታኖል ምርት ሂደት የሚፈበረኩ ማንኛውንም ኬሚካል ለአግሮኖሚ ስራ መጠቀም አይቻልም፤

3/ አንዳንድ በኬሚካል የታሹ ዘሮች የማብላላት ሂደቱን ሊያደናቅፉ ስለሚችሉ በቅድሚያ በጥቂቱ መሞከር ያስፈልጋል፡፡

34. በኬሚካል የታሸ ዘር መቋጠርያ አወጋገድ፤

በኬሚካል የታሸ ዘር መቋጠርያ ከመወገዱ በፊት ሁልጊዜ በተገቢው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካል ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል:-

34.1 ያገለገሉ በኬሚካል የታሹ የዘር መቋጠርያ ለኢንዱስትሪ ለሀይል ምንጭነት መጠቀም፤

34.2 ያገለገሉ መቋጠርያዎችን በተፈቀዱ የቆሻሻ ማቃጠያ (Incinerator) ማቃጠልና የጋዝ ልቀታቸውን በተገቢው ሁኔታ መቆጣጠር፡፡

35. በኬሚካል የታሸ ዘር ወይም በኬሚካል የታሸ ዘር ተረፈ-ምርትን:-

35.1 ለብስባሽ/ኮምፖስት/ መጠቀም በፍጹም የተከለከለ ነው፡፡

35.2 በኬሚካል ከታሹ ዘሮች የሚወጣ ደረጃውን ያላሟላ ያልተጣራ የውሃ ፍሳሽ መጠቀም አይቻልም፡፡

35.3 የኢታኖል ተረፈ-ምርትን ለመኖነት፣ ለእርሻ ተግባር ማዋል፣ ለማገዶ፣ ለምግብ ማብሰያና ማሞቂያ መጠቀም በፍፁም የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## የዘር ጥራት መስፈርትን ያላሟላ ዘር የአስወጋጅ ግብረ-ሓይል አወቃቀርና ሃላፊነት

36. አወቃቀር፤

የዘር ጥራት መስፈርትን ያላሟላ ዘር አስወጋጅ ግብረሃይል የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡ ግብረ-ሓይሉ ስራውን ለመስራት ከግማሽ በላይ አባላቱ መሟላት ይኖርባቸዋል፤ ከተገኙት አባላትም ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት፣ ከጤና ጥበቃ፣ ከደንና ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከገቢዎች፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ እና ከፖሊስ መስሪያ ቤቶች ተወካይ መገኘት ይኖርበታል፤

36.1 በፌደራል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ወይም አግባብ ያለው የክልል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ሰብሳቢ፤

36.2 የፌደራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ፀሀፊ፤

36.3 የፌደራል የመንግስት ንብረት ግዥ አባል፤

36.4 የፌደራል የንግድ ሚኒስቴር ወይም የክልል ንግድ ቢሮ አባል፤

36.5 የፌደራል ወይም የክልል ፖሊስ ኮሚሽን አባል፤

36.6 የአካባቢ፣ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም በክልል የሚመለከተው ባላሥልጣን መሥርያ ቤት አባል፤

36.7 የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ አባል፤

36.8 የፌደራል ወይም የክልል ገቢዎች ባለስልጣን አባል፤

36.9 የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ወይም የክልል እንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ አባል፤

36.10 የፌደራል ወይም የክልል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ አባል፤

36.11 የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር እና በክልል የሚመለከተው ቢሮ አባል፤

36.12. የሚመለከተው የወደቀው ዘር ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ አባል፡፡

37. የግብረ ኃይሉ ኃላፊነት፤

37.1 አግባብ ያለው በፌደራል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት በፌደራል ደረጃ ግብረኃይሉ እንዲቋቋም ይሰራል፤ የግብረ-ኃይሉም ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፤

37.2 አግባብ ያለው የክልል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል የክልል ግብረ-ኃይልን ማቋቋምን በሃላፊነት ተፈጻሚ ያደርጋል፤

37.3 የክልሉ የወደቀ ዘር አስወጋጅ ግብረ-ኃይል እንደአስፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ ደረጃ ተጨማሪ ግብረ-ኃይል ያዋቅራል፤

37.4 የሚወገዱ ዘሮችን በተመለከተ አግባብ ካለው ሚኒስቴር ወይም የዘር ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን መረጃ ወይም ሪፖርት ይቀበላል፣ ይወያይበታል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣ በውሳኔው መሠረት ያስወግዳል፤

37.5 በየወቅቱ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ወይም አግባብ ላለው የክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለቅሬታ አቀራረብ

38. የዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 25 እና ይህን መመሪያ መሠረት ተደርጎ በተሰጠ ማንኛውም ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔውን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ቅሬታውን ውሳኔ ለሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል የተቆጣጣሪው አካል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ማዕከል በአምስት ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

39. አግባብ ያለው የፌዴራል ወይም የክልል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ማዕከል ቅሬታው በደረሰው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

40. በአንቀጽ 39 በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን አግባብ ላለው የፌዴራል ወይም የክልል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በአምስት ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

41. አግባብ ያለው የፌዴራል ወይም የክልል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቅሬታው በደረሰው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

42. ቅሬታ አቅራቢው በባለስልጣኑ በተሰጠው ውሳኔ ካላረካው ቅሬታውን ለሚመለከተው የፍትህ አካል በ30 ቀናት ውሰጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

43. *መመሪያው የሚፈጸምበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ ከ የካቲት 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**እያሱ አብርሃ (ዶ/ር)**
**እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትር**